# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (አንድነት) ልሣን *

ቅጽ 44 ቁ. 3 ነሃሴ 2008


## በጽናትና በኅብረት መቆም ለዓላማ ስኬት

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ከተመሠረተ 44 ራሱን ይፋ ካወጣ ደግሞ 41 ዓመቱ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓ ሲመሠረት ጀምሮ ያነገባቸውና የታገለላቸው ዓላማዎች ዛሬም አንገብጋቢነታቸው አጠያያቂ አይደለም። ዋና ዋናዎቹ በሕዝብ የተመረጠ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት መመሥረት፣ የዜጎች መብቶች ያለገደብ መከበር፣ በነፃነት የመደራጀት መብትና በሕጋዊ መንገድ የዜግነት ግዴታቸውን ማከናወን፣ የብሄረሰቦች ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ የሃይማኖት እኩልነትና የመንግሥት በሃይማኖቶች ጣልቃገብነት መታቀብ፣ የኑሮ ውድነትን የሚቆጣጠርና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ፣ የሴቶችን መብት ማስከበር...ወዘተ የሚሉት በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።*

*ባለፉት አራት አሥርተ-ዓመታት፣ አገራችን በሦስት መንግሥታት አገዛዝ ሥር ያለፈች ሲሆን፣ በየወቅቱ የተነሱት የሕዝብ ጥያቄዎች ግን እስከዛሬ ድረስ ምላሽ አላገኙም። እንዲያውም ፓርቲው ሲመሠረት ያልነበሩ ችግሮች፣ ወይም በመጠናቸውና በዓይነታቸው ቀላል የነበሩ የዚያን ጊዜ ችግሮች ተባብሰውና ሥር ሰደው በሚያሳዝን ደረጃ ፀረ-ሕዝብ ይዘት ኖሯቸው እንመለከታለን። ለምሳሌ በብሄረሰቦች መካከል የነበረውን ወዳጅነትና የኢትዮጵያዊነትን ትስስር በሚያፈርስና በሚያደፈርስ መልኩ አገዛዙ የሚያካሂዳቸው ትንኮሳዎችና ማፈናቀሎች በምሳሌነት የሚጠቀሱ ናቸው። ዛሬ በአገራችን ያለውን ሁኔታ ፓርቲው ሲታወጅ ጀምሮ ከታገለላቸው አቋሞችና ፖሊሲዎች አንፃር ብናመዛዝን፣ ወደኋላ መሄዳችንን ፍንትው አድርገው ስለሚያሳዩ ዘርዘር አድርገን እንመልከታቸው።*

1ኛ. *<u>በሕዝብ ፈቃድና ይሁንታ የሚመሠረት መንግሥት ጥያቄ፡</u> የደርግ አምባገነን መንግሥት የተለያዩ የሕዝብ ክፍሎች ማለትም፣ የሠራተኛው ማኅበር፣፤ የመምህራንና የተማሪዎች ማኅበራት፣ የጭቁን ወታደሮችና የሴቶች እንዲሁም የገበሬዎችና በአጠቃላይ የመንግሥት ሠራተኞች ስብስብ አበክረው የሲቪል መንግሥት በሕዝብ ምርጫ*

እንዲመሠረት ጥያቄ ቢያቀርቡም፣ አሻፈረኝ አለ። ሌላው ቀርቶ፣ ራሱ ደርግ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ያጫቸው ዜጎች፣ እንደ አቶ ሐዲስ ዓለማየሁና ልጅ ሚካኤል እምሩ ዓይነቶቹ የሰጡትን የሕዝባዊ መንግሥት መመሥረት ምክርና ከራሱ ከደርግም ውስጥ ከማንኛውም ፓርቲ ጋር ያልወገኑ የአገሪቱ ርዕሰ-ብሄር ጀኔራል ተፈሪ በንቲ ያቀረቡትን የመቻቻል ፖለቲካ ከመጤፍ ባለመቁጠሩ፣ በአገሪቱ የደረሰውን ሁኔታ ያኔ የነበረ ልብ በሚነካ አሳዛኝ ትዝታ የሚያስታውሰው ነው። አዲሱ ትውልድም ዛሬ በመራራ ታሪክነቱ የሚገነዘበው ሃቅ ነው። በደርግ ምትክ የተተከለው የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ በግብር ከደርጉ ጋር አንድ ሆኖ በፖለቲካ ተንኮሉ ግን የውጭ መንግሥታትን ዳረጎት ለማግኘት ሲል በየአምስት ዓመቱ የሚያደርጋቸው የይስሙላ ምርጫዎች ባለፉት 25 ዓመታት ራሱን መልሶ መላልሶ ወደ ሥልጣን ከማምጣት ውጭ የፈየደው ነገር የለም። አሁን በአገራችን የሚታየው ሕዝባዊ ቁጣና አመፅ ከመከሰቱ በፊት ድርጅታችን ኢሕአፓ (አንድነት)ና ሌሎች ድርጅቶችም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች በሰላማዊና በብሄራዊ እርቅ ዙሪያ እንዲፈቱ ለዓመታት አበክረን ስናሳስብ የኖርነው ጉዳይ ነው። ሰሚ ጠፍቶና ህወሓታዊ ትምክህትና የበላይነት ስሜት በአገዛዙ ዙሪያ በመንሰራፋቱ፣ አገዛዙ በተያያዘው የጥፋት ጎዳና ቀጥሎበታል። ስለዚህም ነው ሕዝባችን አሁን እያደረገ እንዳለው በቃኝ ብሎ መብቶቹን የሚያስከብርለትን ከራሱ የፈለቀ መንግሥት እስኪመሠረት ድረስ ትግሉን አምርሮ በጽናት መቀጥል የሚኖርበት።

2ኛ. የሕዝብ በነፃ የመደራጀት መብት አለመከበር፡ ደርግ ፓርቲያችን በሕገ-ወጥነት ፈርጆ እንዳሳደደውና ሌሎች የሕዝብ ክፍሎችንም እንደዚሁ የሱ ደጋፊ ካልሆኑ በስተቀር በሰላማዊ መንገድ መኖር ባለመቻላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለያየ መንገድ እስከትጥቅ ትግል ድረስ በመደረሱ ደርግ አስከፊ እልቂት አደርሶ፣ ሀገራችንን መውጣት ከማትችልበት አዘቅት ውስጥ ከቷት አልፏል። በዛሬውም የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ፣ ነፃ የሠራተኛ ማኅበር፣ ነፃ የመምህራን ማኅበር፣ በራሱ የተደራጀና ነፃ የሆነ የተማሪዎች ማኅበር፣ ነፃ የመገናኛ ብዙኃንና በራሳቸው እግር መቆም የቻሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች…ወዘተ ማቋቋም ማሰብ የማይቻል ሆኗል። በአንፃሩ፣ በህወሓት አደረጃጀት ለተመልካች ነፃ የሚመስሉ ሆኖም ግን፣ እሱው እንደጭቃ ጠፍጥፎ የሠራቸው ተለጣፊ ድርጅቶች ግዑዝ ፍጥረታት እንደሆኑ ሕዝባችን ያውቃል። የህፍረተ-ቢስነቱ ቁንጮ ሆኖ የተሰየመው የይስሙላ ፓርላማ አባላት በሞላ የህወሓት/ኢህአዴግ ፓርቲ አባሎች መሆናቸው፣ በይዘት ከደርግ ጋር አንድ ለመሆናቸው ጉልህ ማስረጃ ነው።

3ኛ. <u>የብሄረሰቦች ሙሉ መብት መከበር ጉዳይ፡</u> ድርጅታችን ኢሕአፓ በመርሀ-ግብሩና በአራት አሥርተ-ዓመታት የትግል ዘመኑ፣ የብሄረሰቦች መብት እንዲከበር ያላሰለሰ ትግል አድርጓል፣ መስዋዕትነትም ከፍሏል። ደርግ በጦርነት ብቻ ይፈታል ብሎ አክራሪ አቋም በወሰደ ጊዜ ኢሕአፓ በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ ብሎ ታግሏል። በማርክሳዊ ርዕዮተዓለም በሚመራበት ጊዜም ቢሆን፣ ዓላማው የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች ሙሉ መብት ቢታወቅ፣ "እንገንጠል" የሚሉ አክራሪ ክፍሎች መብታቸውና እኩልነታቸው በተራማጅ ሥርዓት ከተረጋገጠ፣ ጽንፈኛ ጥያቄዎቻቸው አድሃሪና ፋይዳቢስ እንደሚሆን አስረግጧል። ከዚያም ወዲህ ኢሕአፓ መርሃ-ግብሩን አሻሽሎ፣ ብሄረሰቦች የውስጥ አስተዳደራቸውና ባህላዊ እሴቶቻቸውን የማስከበር መብታቸው በሚታወቀባት በአንዲት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ ለመኖር ያላቸውን ፍላጎትና ፍቃድ አስምሮበታል። ይህም ሃቅ ባለፉት ሁለት አሥርተ-ዓመታት ህወሓት እየመረረውም ቢሆን እንዲቀበለው ስለተገደደ "ከጳጳሱ በላይ ሃይማኖተኛ" እንዲሉ "የባንዲራ ቀን" እያለ ለማጭበርበር ሞክሯል። በተግባር ግን አንቀጽ 39ን የመሰለ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት አንቀጽ ሕገ-መንግሥት ተብየው ውስጥ አስገብቶ እንደ አኙዋክና አማራ የመሳሰሉትን ብሄረሰቦች ለረጅም ዓመታት ከኖሩበት ቀየ በጭቃ ሹሞቹ አማካኝነት እያፈናቀለ፣ የኦሮሞና የሶማሌ ተወላጅ የሆኑትንም በእሥር ቤቶቹ እያማቀቀ፣ ለብሄረሰብ መብት የቆምኩ ነኝ እያለ ያፌዛል። ህወሓት፣ አገሪቱን በጎሣ ከፋፍሎ በጭፍን የቡድን ስሜት የሚመራ አካል በመሆኑ፣ በዚሁ ጠባብ ጎሣዊ ዕይታ ተመርቶ በታሪክ የጎንደር ክፍል የሆኑትን ወልቃይትን፣ ጠገዴንና ጸለምትን ወደ ትግራይ በማካለል፣ ኢ-ሰብአዊ የሆነ ጭፍጨፋ ከማድረጉም በላይ ወንድማማችና እህትማማች የሆኑትን፣ ተጋብተውና ተዋልደው የሚኖሩትን የትግሬና የጎንደር ሕብረተሰቦችን በማመስ ላይ ይገኛል።

ካለፉት በርካታ ወራት ጀምሮ በደቡብ ምሥራቅና በሰሜን ምዕራብ አካባቢ ሕዝብ እየተካሄደ የሚገኘው ፀረ-ህወሓት/ኢህአዴግ ፀረ-አምባገነናዊ ትግል የችግሩን ጥልቀት አመላካች ከመሆንም በላይ የነፃነት ተስፋ ፈንጣቂም ነው።

4ኛ. <u>የሃይማኖቶች እኩልነትና መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አለመግባት፡</u> ኢሕአፓ የሃይማኖችን እኩልነትና መንግሥትና ሃይማኖትን የመለያየት ፅንሰ-ሃሳብ ገና ከጥዋቱ ጀምሮ የታገለለት ዓላማው ነው። በተለይም በታሪካችን የእስልምና ሃይማኖት ለዘመናት አድሎ የተደረገበት ሃይማኖት ስለነበረ፣ የእስልምና በዓላት እንደ ክርስቲያን በዓላት በብሄራዊ ደረጃ እንዲከበሩ ከሙስሊምና ከተራማጅ ክርስቲያን ወገኖቹ ጋር አብሮ ታግሎ ለተግባራዊነቱ አስተዋጽዖ አድርጓል። ህወሓት/ኢህአዴግ "ከኔ በላይ ለአሳር" እያለ

ሲፎክር ከሰነባበተ በኋላ፣ ፈታኙ ወቅት የመጣበት ባለፉት ጥቂት ዓመታት ነው ማለት ይቻላል። እንደልማዱ የጻፈውን ሕገ-መንግሥት ተብዬውን በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ የሚለውን ወደጎን ትቶ፣ ሙስሊሙን ኅብረተሰብ "የሚበጃችሁን እኔ አውቅላችኋለሁ" በማለት መንግሥት ተብዬው በሃይማኖት ጣልቃ መግባቱ ግልጽ ነው። የሙስሊሙም ኅብረተሰብ አታውቅልንም፣ እኛው በራሳችን መንገድ ሃይማኖታችንን እንመራለን፣ የሚመሩንንም ሰዎች እኛው መክረን ዘክረን በነፃነት እንመርጣለን" በማለት፣ እነሆ ትውልድን በሚያኮራ መልኩ ለዓመታት ያልተቋረጠ ሰላማዊና መንፈሳዊ ትግል አድርገዋል፣ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ። በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ቢያቀርቡም፣ ለጥያቄያቸው ተገቢውን መልስ ከመስጠት ይልቅ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመረጧቸውን ተወካዮቻቸውን ያለፍርድ ወህኒ ወርውሯቸዋል። ይህ የሙስሊም ወገኖቻችን ትግል ከአጠቃላይ የዴሞክራሲና በሰላማዊ መንገድ ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ከሚደረገው ትግል ጋር መቆራኘት እንደሚገባው ሁኔታው ግድ ይላል። በዚህ በኩል አገር ቤት ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራትና ወጣቶች ህወሓት/ኢህአዴግ በሚያስተጋባው የሃሰት "የአሸባሪነት" ፕሮፓጋንዳ ሳይደናገጡ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል በአንድ መስመርና አቅጣጫ ማስኬድ የወቅቱ ግዴታቸው መሆን ይገባዋል።

5ኛ. <u>ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲና የኑሮ ውድነት ጉዳይ፡</u> ኢሕአፓ በትግል ታሪኩ ከደሃው ኢትዮጵያዊ ጋር የወገነ፣ ድህነትና ረሃብ ከአገራችን እንዲወገዱ በግምባር ቀደምነት የታገለና ዛሬም የሚታገል ፓርቲ ነው። የባላባታዊ ሥርዓትን ያስወገደውን የመሬት አዋጅ ካረቀቁትና ካስፈጸሙት ተራማጅ ወገኖች መካከል የኢሕአፓ አባላትም ይገኙበት ነበር። ሆኖም ደርግ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ሁሉ በሱ አምሳል ለመቅረጽ በማደራጀቱና ቢሮክራሲያዊ አሠራሩ ይህ አዋጅና ሌሎችም የተደነገጉ ፖሊሲዎች ሊያስገኙ የሚችሉትን ያህል እንዳይገኝ በማድረጉና አገሪቷም በጦርነት በመታመሷ ድህነትና ረሃብ የሀገራችን መታወቂያዋ ሆነዋል። ህወሓት/ኢህአዴግ "ልማታዊ መንግሥት" ነኝ እያለ ራሱን ቢያሞካሽምና ኤኮኖሚውም ፈጣን ዕድገት እያሳየ ነው ቢልም አገራችን በድህነትና በረሃብ ላይ እንደምትገኝና የኑሮ ውድነትም እጅግ ከግምት ውጪ መሆኑ ፀሐይ የሞቀው ሃቅ ነው። ህወሓት አገሪቱን ወደብ አልባ በማድረግ በየዓመቱ ለጎረቤት አገሮች የወደብ ኪራይ የሚወጣውን በቢሊየን የሚቆጠር ገንዘብ ልብ ብሎ መመርመር ይገባዋል። ለውጭ ባለሀብቶች በርካሽ የሚቸረችረውን የአገሪቱን ለም የእርሻና የደን መሬት ጉዳይም የሀገር ጥቅምን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ መስተካከል አለበት እንላለን። ዛሬ በአገሪቱ ተንሰራፍቶ በየሚገኘው ሙስና የገኘው ፓርቲ ከላይ እስከታች የተዘፈቀበት ነው።

የአገሪቱን ሀብት ጥቂት ምርጦች “ኤፈርት” በሚል ሰበብ በአገር ውስጥና በውጭ አገር ባንኮች የሚያካሂዱት ዓይን ያወጣ ዘረፋ የምናየውና የምገነዘበው ስለሆነ የዚህ ዓይነት ሙስና በተስፋፋበት አገር “ልማታዊ ጋዜጠኛ”ና “ልማታዊ ሀብታም” ድህነትንና ረሃብን ለማጥፋት ጨርሶ እንደማይሰለፉ የታወቀ ነው።

6ኛ. <u>የሴቶች መብት መከበር ጉዳይ፡</u> ኢሕአፓ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ሴት እህቶቻችንና እናቶቻችንን ትግሉን እንዲቀላቀሉ ከማድረጉም በላይ በፓርቲው ውስጥ ሴቶች የጎላ ሚና እንዲጫወቱ አድርጓል። በገጠሪቷ ኢትዮጵያ ለአቅመ-ሄዋን ያልደረሱ ልጃገረዶች ባህላዊ ጋብቻ እንዲቀር የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል። ሴቶች ሠራተኞች ከወንዶች ሠራተኞች እኩል የደመወዝ ክፍያ እንዲያገኙም ታግሏል። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ እነሆ ዛሬ የሴቶች መብት በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ይገኛል። በሥራ ማጣት ምክንያት ሴቶች አካላቸውን እንዲሸጡ የሚገደዱበት ኢ-ሰብዓዊ ሁኔታ በከፋና በአስቃቂ መልኩ ተስፋፍቷል። በኑሮ ውድነቱ ሳቢያ ብዙ እናቶች ልጆቻቸውን ማሳደግ ባለመቻላቸው በማደጎነት ለውጭ ዜጎች መስጠት/መሸጥ የተለመደ ሁኗል። እነዚህም ሕፃናትም ሥነ-ምግባር በጎደላቸው አንዳንድ የውጭ ዜጎች እንደሚበደሉና ይባስ ብሎም እንደሚገደሉ በመሪር ሃዘን እየሰማን ነው። ወጣት ሴቶች ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ለሥራ እየሄዱ እጅግ በሚያሳዝን ውርደት እየተሰቃዩ እንደሚገኙ ይታወቃል። ሴትና ወንድ ወጣቶች ከአገር እየተሰደዱ በወጡ ቁጥር የበረሃና የባህር አውሬ ቀለብ የሚሆኑት በርካታ ናቸው። እንግዲህ የዛሬይቱ ኢትዮጵያችን ዕድሜ ለህወሓት ይህን የመሰለ መልክ ያላት አገር ሆናለች። ይህ ግን የማይለወጥ ቋሚ ሃውልት አይደለም፤ ሊሆንም አይገባውም። የሥልጣን ምንጭ የሆነው ሕዝባችን መብቱን ለማረጋገጥ በሰሜን በደቡብ፣ በምሥራቅና በምዕራብ በአጠቃላይ በአራቱም ማዕዘናት በየሚፈለገውን መስዋእትነት እየከፈለ ባለበት በአሁኑ ወቅት፣ ሴቶች እናቶቻችንና እህቶቻችን ትግሉን በመቀላቀል ከሰላማዊ ትግል እስከ መሣሪያ አንግቦ መፋለም ድረስ በመሳተፍ፣ እንዲሁም የእናትነትና የእህትነት የዕርዳታ ግዴታቸውን ለመወጣት ለሰልፈኛው ስንቅ በማቅረብና ውሃ በማጠጣት ድርሻቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።

<u>7ኛ. በኅብረት ግምባር ስለመታገል አስፈላጊነት፦ </u>ኢሕአፓ ደርግ በሥልጣን ላይ እያለ ላቀረበለት የይስሙላ በግምባር የመሳተፍ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ፣ “ኢሕአፓ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም የብሄረሰቦችና አገር አቀፍ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ዴሞክራሲያዊ ግምባር እንዲመሠረት ይሁን" ብሎ በማሳሰብ ነበር። ደርግ ግን ሃሳቡን ውድቅ አድርጎ፣ ኢሕአፓ ላይ ጦር ከመዘዘ በኋላና ራሱም ከወደቀ በኋላ፣ ድርጅታችን የዛሬ 25 ዓመት አካባቢ

የመጀመሪያውን ሰፊና የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያካተተውን የኅብረት ግምባር፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅትን (ኢዴኃቅ)ን ከመሠረቱት ድርጅቶች አንዱ ነበር። ከዚያ በኋላ በተመሠረቱት የኅብረት ግምባሮችም - የዛሬውን ሸንጎ ጨምሮ - ኢሕአፓ (አንድነት) በጋራ የመታገልን አስፈላጊነት በንድፈ ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባር፣ በንቁ ተሳታፊነት የሚገኝበት ነው።

ዓመታት እያለፉና ትውልድ በትውልድ እየተተካ ሲሄድ፣ ኢሕአፓ የትግሉን የዱላ ቅብብሎሽ ለአዲሱ ትውልድ ማስረከቡን ከሚያመላክቱት መንገዶች አንዱ አባሎቹ በወጣትነት ዕድሜያቸው ያነሷቸውን ጥያቄዎች ዛሬም እነሱን አንስቶ የሚታገልና መስዋዕትነት የሚከፍል አዲስ ትውልድ መከሰቱ ነው። "እሰየው ወላድ በድባብ ትሂድ" ትግሉ ያብብ፣ ይለምልም፣ ይዛመት የሚያሰኝ ነው። ኢሕአፓ (አንድነት) ከዛሬዎቹ ወጣቶች ጎን ቆሞ ተመክሮውን ማካፈል ብቻ ሳይሆን፣ እንደትናንቱ በትግሉም አብሮ በጽናት ይቀጥላል።

ኢሕአፓ አበክሮ የጠየቃቸውና የታገለላቸው ከላይ የተጠቀሱት የሕዝብ ጥያቄዎች እስከዛሬ ድረስ ሕያው የሕዝብ የመታገያ ዓላማ ሆነው ቀጥለዋል። የህወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝም ጥያቄዎቹን አግባብ ባለው መንገድ ከመመለስ ይልቅ ለራሱ በሚጠቅመው መንገድ የበለጠ እያወሳሰባቸው በመሄዱ፣ ጭቆናና ግፍ ያንገፈገፈው ሕዝብ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ሆ! ብሎ ተነስቶ ህወሓትን እያርበደበደው ይገኛል። የተነቃነቀ ጥርስ ካልወለቀ አይድንምና፣ ይህ ሕዝባዊ አመፅ የህወሓት/ኢህአዴግን አገዛዝ ነቅሎ መጣል አለበት እንላለን። ኢሕአፓ (አንድነት) ዛሬም እንደ በፊቱ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን መቆሙን በድጋሚ ያረጋግጣል።

አገራችን አሁን ያለችበት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንና የተቃዋሚ ድርጅቶች ልዩነቶቻችንን አቻችለን በአንድነትና በኅብረት አገራችንና ሕዝባችንን እንድንታደግ ኢሕአፓ (አንድነት) አገራዊ ጥሪውን ያቀርባል።

አሻፈረኝ ብሎ በአንድነት የተነሳ ሕዝብ ያቸንፋል!